**በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**
**የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት**

የሠ/መ/ቁጥር 246305

ታሕሳስ 25 ቀን 2016ዓ/ም

**ዳኞች ፡- ብርሃኑ አመነዉ**

**በዕዉቀት በላይ**

**ቀነዓ ቂጣታ**

**ብርሃኑ መንግሥቱ**

**ማርታ ተካ**

**አመልካች ፡-** የኢትዮጵያ ግብርና ባለሥልጣን — አልቀረቡም

**ተጠሪ -** አቶ በቀለ ጀመረ

መዝገቡ ለዛሬ የተቀጠረዉ ለምርመራ ሲሆን ተጠሪ በምዕራብ ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአመልካች ላይ በመሰረቱት ክስ አመልካች ከሕግ አግባብ ዉጭ ገፍቶ አጥር በማጠር የያዙብኝነት 2½ ሄክታር የዕርሻ መሬት አጥሩን አፍረሶ እንዲለቅ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ አመልካች የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎችን በማስቀደም በሰጠዉ ዉሳኔ ካሳ ከፍዬ ተፈቅዶልኝ ከያዝኩት መሬት ዉጭ የተጠሪን የእርሻ መሬት አልያዝኩም በማለት ክሱ ዉድቅ እንዲደረግለት በመጠየቅ ተከራክሯል፡፡ፍርድ ቤቱም የአመልካችን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በብይን ዉድቅ ካደረገ በኋላ ፍሬ ነገሩን በተመለከተ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃዎችን መርምሮ በመ/ቁጥር 0000737 ላይ በቀን 03/09/2013ዓ/ም በሰጠዉ ፍርድ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

አመልካች ገፍቶ ያጠረዉ የተጠሪ የመሬት ይዞታ የለም በማለት ክሱን ዉድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡ተጠሪ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ቢያቀርቡ አመልካችን ሳይጠራ ሰርዞባቸዋል፡፡በመቀጠል አመልካች ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት መርምሮ በመ/ቁጥር 114555 ላይ በሰጠዉ ፍርድ ክሱ ከገጠር መሬት ይዞታ ጋር የተያያዘ አለመግባባትን የሚመለከት በመሆኑ በክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 252/2009 አንቀጽ 52 እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በተለያዩ መዛግብት ላይ በሰጠዉ የሕግ ትርጉም መሰረት ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ዳኝነት ሥልጣን ተቀብሎ መዳኘት የሚችለዉ የወረዳ ፍርድ ቤት እንጂ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ስላልሆነ የሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የስረ ነገር ዳኝነት ሥልጣን የለዉም በማለት ሽሯል፡፡

አመልካች በቀን 28/07/2015ዓ/ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረበዉ፡- 1) ግራ ቀኝ ነዋሪነታችን በተለያየ ክልል በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 5(1/ሸ) መሰረት ጉዳዩን የመዳኘት ሥልጣን የፌዴራል ፍርድ ቤት ነዉ፡፡2) በሰ/መ/ቁጥር 144613 እና 139942 ላይ በተሰጠዉ የሕግ ትርጉም መሰረት የአካባቢ ዳኝነት ሥልጣን የወረዳ ፍርድ ቤት ቢሆን እንኳን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና ጠቅላይ ፍርድ ቤት ጉዳዩን መዳኘት እንደሚችሉ ወስኗል፡፡3)ከዚህ ቀደም ተጠሪ በወረዳ ፍርድ ቤት ክስ መስርተዉ ፍርድ ቤቱ ሥልጣን የለኝም በማለት መዝገቡ እንዲዘጋ የሰጠዉ ዉሳኔ እስካሁን ጸንቶ የሚገኝ የክልሉ ሰበር ችሎቱ ክርክሩ በወረዳ ፍርድ ቤት መታየት አለበት ብሎ ሲወስን አንድ ጉዳይ ሁለት ጊዜ መታየት የለበትም በሚል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 5 ስር የተደነገገዉን መርህ እና በሰ/መ/ቁጥር 85718 እና 193383 ላይ የተሰጠዉ የሕግ ትርጉም የሚቃረን በመሆኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ በማለት ከጠቀሳቸዉ ምክንያቶች ዉስጥ የሰበር አጣሪ ችሎት በተራ ቁጥር 1 እና 2 የተጠቀሱትን ምክንያቶች በመቀበል ጉዳዩን ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት በመምራቱ ችሎቱም አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ የሚከተለዉን ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

## ት እ ዛ ዝ

በኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 50/1 ሥር እንደተደነገገዉ በአገራችን የተመሰረተዉን የፌዴራል ሥርዓት ተከትሎ የፌዴራል መንግሥትና ክልሎች የየራሳቸዉ የሕግ አዉጪነት፣የሕግ አስፈጻሚነትና የዳኝነት ሥልጣን አላቸዉ፡፡በዚህ መሰረት በሕገ መንግሥቱ የተወሰነዉን የሥልጣን ክፍፍል መከተል ይገባል፡፡በሌላ አገላለጽ ለፌዴራሉ መንግሥት የተሰጠዉን ሥልጣን ክልሎች ማክበር ፤ለክልሎች የተሰጠዉንም ሥልጣን የፌዴራሉ መንግሥት ማክበር እንዳለበት በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 50/8 ስር ተደንግጓል፡፡በዚህ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 52(2/መ) ላይ እንደተመለከተዉ መሬትና የተፈጥሮ ሀብት በፌዴራል መንግሥት በሚወጣ ሕግ መሰረት የማስተዳደር ሥልጣን የክልሎች ሥልጣን ነዉ፡፡በገጠር የእርሻ መሬት የመጠቀም መብት ስለሚገኝበትና መብት ስለሚተላለፍበት አግባብ በተመለከተ የፌዴራል መንግሥት የገጠር መሬት አስተተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 456/1997 ያወጣ ሲሆን በዚህ አዋጅ አንቀጽ 17 ስር አዋጁን ለማስፈጸም ክልሎች የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ሕግ ሊያወጡ እንደሚችሉ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በግልጽ ተመልክቶአል፡፡በዚሁ አዋጅ ቁጥር 456/1997 አንቀጽ 12 ስር የገጠር መሬት ይዞታ መብትን በተመለከተ የሚነሳ ክርክር የሚወሰነዉ ክልሎች በሚያወጡት የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ መሰረት እንደሆነ ተደንግጓል፡፡

በኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 80/1 እና በተሻሻለዉ የአማራ ክልል ሕገ መንግሥት አንቀጽ 67(2/ሀ) ስር እንደተመለከተዉ ክልላዊ ጉዳዮችን በተመለከተ ከፍተኛዉና የመጨረሻዉ የዳኝነት ሥልጣን የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ነዉ፡፡በኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 78/3፣ በክልሉ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 67/1 እና በተሻሻለዉ የአማራ ክልል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 281/2014 አንቀጽ 5/1 ስር እንደተመለከተዉ የክልሉ የዳኝነት አካል በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣በከፍተኛ ፍርድ ቤቶችና በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶች እንደሚደራጅና የወረዳዉ ፍርድ ቤት የክልሉ የበታችና የመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት አካል እንደሆነ ተደንግጓል፡፡ይህንን ክልላዊ የሆነዉን ዳኝነታዊ የሥልጣን ክፍፍል የፌዴራል ፍርድ ቤቶች እንዲያከብሩና እንዲያስከብሩ ሕገ መንግሥቱ ያስገድዳል(የኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 9/2 እና 50/8 ይመለከቷል)፡፡

የፍትሐ ብሔር ክርክር በመርህ ደረጃ የሚመራዉ በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ በተዘረጋዉ ሥርዓት መሰረት ቢሆንም በልዩ ሁኔታ በፌዴራልም ሆነ በክልል ፍርድ ቤቶች አዋጆች ላይ እና በሌሎች በፌዴራልና በክልል ደረጃ በወጡ ልዩ ሕግጋት ላይ የተደነገጉ ሥነ ሥርዓታዊ ደንቦች በፍትሐ ብሔር ክርክር አመራር ሒደት ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡በአማራ ክልል የገጠር መሬት አጠቃቀምና አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 252/2009 አንቀጽ 52 ላይ የገጠር መሬት የይዞታና የመጠቀም መብት በተመለከተ የሚፈጠሩ አለመግባባቶች ወይም የሚነሱ ክርክሮች ታይተዉ ስለሚወሰኑበት እና የይግባኝ አቀራረብ ሥነ ሥርዓት በተመለከተ በዝርዝር ተደነግጓል፡፡በዚህ አዋጅ አንቀጽ 52/2 ስር በተደነገገዉ መሰረት የገጠር መሬት የይዞታና የመጠቀም መብት አስመልክቶ የሚነሳ አለመግባባት በመጀመሪያ ደረጃ ዳኝነት ሥልጣን ተቀብሎ እንዲዳኝ ሥልጣን የተሰጠዉ ለክልሉ የወረዳ ፍርድ ቤት ነዉ፡፡

በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ተወስኖ የሚሰጥ አስገዳጅ ትርጉም በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10/4 (በአዋጅ ቁጥር 454/1997 እንደተሻሻለዉ) እና ይህንን አዋጅ በተካዉ አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 10/2 መሰረት በየትኛውም ደረጃ ላይ በሚገኙ ፍርድ ቤቶች ዘንድ አስገዳጅነት ኖሯቸዉ ተፋጻሚ መሆን ያለባቸዉ ዉሳኔ ከሚፈልገዉና አከራካሪ በሆነዉ ተመሳሳይ ጉዳይ ላይ *(ratio decidendi - the point in a case that determines the judgement)* የተሰጠ የሕግ ትርጉም ሲሆን ነዉ፡፡ በሰ/መ/ቁጥር 139942(በቅጽ 22 በታተመዉ) እና በሰ/መ/ቁጥር 144613 (በቅጽ 23 በታተመዉ) ላይ የተሰጠዉ የሕግ ትርጉም እንደቅደምተከተላቸዉ የከተማ ቤት ባለሀብትነትን በመፋለምና በከተማ ቤት ላይ የተቋቋመ የሽያጭ ዉል መነሻ የደረጉ ክሶችን ጋር በተያያዘ በክልልና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነዋሪ በሆኑ ሰዎች መካከል የሚደረግ ክርክር የመዳኘት ሥልጣን እና የግዛት ክልል ዳኝነት ሥልጣን (local jurisdiction) በሚመለከት የተሰጠ የሕግ ትርጉም ነዉ፡፡የተያዘዉ ጉዳይ ደግሞ በክልሎች የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ላይ የተመለከተዉን የዳኝነት ሥልጣን እና በክልልና በአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ በሆኑ ሰዎች መካከል ወይም የፌዴራል መንግሥት አካል እና በክልል ነዋሪ መካከል የገጠር መሬት ይዞታ ከመፋለም ጋር በተያያዘ የተነሳ ክርክር የመዳኘነት ሥልጣን አስመልክቶ የተሰጠ የሕግ ትርጉም ካለመሆኑም በተጨማሪ ይህ ጉዳይ ለተያዘዉ ጉዳይ እንደአስገዳጅ የዉሳኔ ክፍል (*ratio decidendis)* ስለማይቆጠር ተፈጻሚነት ያለዉ አይደለም፡፡

ይልቁንም በሁለት ክልሎች(የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርን ጨምሮ) ነዋሪዎች መካከል ወይም በክልል ነዋሪና በፌዴራል መንግሥት አካል/በፌዴራል ተመዝጋቢ መካከል የገጠር የእርሻ መሬት የይዞታ መብት ይገባኛል በሚል የሚቀርብ ክስ የገጠር መሬት ከማስተዳደር ጋር የተያያዘዉን የክልል ጉዳይ የሚመለከት

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

እንደመሆኑ የክልል ሕግ አዉጪ የወሰነዉን የዳኝነት ሥልጣን ክፍፍል በጠበቀ አኳኋን ተከራካሪ ወገኖች በተለያዩ ክልሎች ነዋሪ መሆናቸዉ ከግምት ሳይገባ በመጀመሪያ ደረጃ ዳኝነት ሥልጣን ሊዳኝ የሚገባዉ በክልል የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ላይ በተመለተዉ የዳኝነት ሥልጣን ክፍፍል መሰረት በወረዳ ፍርድ ቤት ነዉ በማለት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ//ቁጥር 106560፣ 116583፣ 112464 እና በሌሎችም መዛግብት ላይ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡ በመሆኑም የክሱ ስረ ነገር የገጠር መሬት ይዞታ መብትን የሚመለከት ክርክር እስከሆነ ድረስ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 5(1/ረ፣ሸ እና ተ) ስር ከተከራካሪ ወገኖች አንዱ የሌላ ክልል ነዋሪ መሆን ወይም የፌዴራል መንግሥት አካል ወይም ተመዝጋቢ መሆን አስመልክቶ የተደነገገዉም በእነዚህ መዛግብት ላይ የተጠቀሰዉን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ባገናዘበ መልኩ ተፈጻሚ ሊሆን ይገባል፡፡

ሲጠቃለል በተያዘዉ ጉዳይ የክሱ ሥረ ነገር እና የክሱ ምክንያት የገጠር መሬት የመጠቀም ወይም ይዞታ መብት መፋለምን የሚመለከት በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 456/1997 አንቀጽ 12 እና 17 እንዲሁም በክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 252/2009 አንቀጽ 52/2 መሰረት ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ዳኝነት ሥልጣን ለመዳኘት ሥልጣን ያለው የወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ ከተከራካሪ ወገኖች አንዱ የሌላ ክልል ነዋሪ መሆኑ ወይም የፌዴራል መንግሥት አካል ወይም ተመዝጋቢ መሆኑ ጉዳዩን በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የሥረ ነገር ስልጣን ስር እንዲወድቅ የሚያደርገው አይደለም፡፡እንዲሁም ተጠሪ አስቀድሞ በሌላ መዝገብ ላይ ለወረዳ ፍርድ ቤት ክስ አቅርቦ የወረዳዉ ፍርድ ቤት ሥልጣን የለኝም በማለት መወሰኑ ተጠሪ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰጠዉ ዉሳኔ መሰረት ለወረዳ ፍርድ ቤት ክስ ሲያቀርብ የመጨረሻ ዉሳኔ በተሰጠበት ጉዳይ ላይ ለሁለተኛ ጊዜ እንደቀረበ ክስ ሊቆጠር ይገባልን? ተጠሪ ሥልጣን የለኝም ብሎ ዉሳኔ ለሰጠዉ ለወረዳ ፍርድ ቤት ክሳቸዉን ከማቅረባቸዉ በፊት ሊጠይቁ የሚገባቸዉ ሌላ ሥነ ሥርዓታዊ መፍትሔ መኖር አለመኖሩን? በተመለከተ በተያዘዉ መዝገብ ላይ ዉሳኔ መስጠት ሥነ ሥርዓተዊ ባለመሆኑ አልመረመርንም፡፡ ስለሆነም የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 114555 ላይ በቀን 28/06/2015ዓ/ም የዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ዳኝነት ሥልጣን ለመዳኘት ሥልጣን የለዉም በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ ሕግንና ከላይ በተጠቀሱት መዛግብት የፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠዉን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም መሰረት ያደረገ በመሆኑ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4/ሀ፣ለ እና ሸ) እና 10(1/ሐ እና መ) ስር በተደነገገዉ መሰረት በዚህ ችሎት ደረጃ ሊታረም የሚችል መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ባለመሆኑ ተጠሪን መጥራት ሳያስፈልግ በሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 7/1 ስር በተደነገገዉ መሰረት የሰበር አቤቱታዉን ዉድቅ አድርጓል፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፅ/ወ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !